## ከ ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ

# ግልጽ ደብዳቤ ለ ዶ/ር በያና ሱባ

ይድረስ ለተክበሩ ዶ/ር በያና ሱባ፣ የኦሮሞ ዲሞክራሲ ግንባር አመራር አባል በአሉበት።

ይህን ደብዳቤ እንድ ጽፍልዎት ያነሳሱኝ ምክንያቶች ርስዎ በቅርቡ ለኢሳት ሬዲዮ የሰጡት ቃለመጠይቅ እና አሁን ርስዎ የሚመሩት ከሳምንታት በፊት የተቋቋመው "የ ኦሮሞ ዲሞክራቲክ ግንባር" የወሰዳቸው አቋሞች ናቸው። የርስዎ ቃለመጠይቅና የግንባሩ አዲስ አቋሞች በግሌ እንደ አስደሰቱኝ በዚህ አጋጣሚ ልገልጽልዎ እወዳለሁ።

ለኔ እንደሚገባኝ፣ አዲሱ ግንባራችሁ የኦሮሞን ህዝብ እና የእናንተንም ኢትዮጵያዊነት ያለማወላወል አምኖ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ሃገርም "ኦሮምያ" የተባለችው ጠባብ ምድር ብቻ ሳትሆን መላዋ ኢትዮጵያ መሆኑን ተቀብሎ፣ የኦሮሞን ህዝብ ዕጣ ፈንታ ከ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር አጣምሮ ለመታገል አብስሯል። ይህም አቋም ለኦሮሞ ህዝብ ታላቅ የፖለቲካ እመርታ ነው። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከጥንቱ፣ ከጠዋቱ፣ ከጥንስሱ ይህን ጥርት ያለ አቋም ይዞ ቢሆን ኖር  ምናልባት ዛሬ ኢትዮጵያን የሚመራት እሱ በሆነ ነበር። የመላውን የኢትዮጵያ ህዝቦች ድጋፍና ትብብር ያገኝ ነበርና። ከዚህም በላይ ያ ሁሉ ደም ላይፈስ፣ ያ ሁሉ ሰው ላይፈናቀል፣ ላይሰደድና ለእስር ላይዳረግ በቻለ ነበር።

ርግጥ ለ ኦሮሞ ዝርያዎች በግለሰብ ደረጃም ሆነ አልሆነ ኢትዮጵያን መምራትና ማስተዳድር አዲስ ክስተት አይደለም። ከዛሬ 3500 ዓመታት ጀምሮ ይህን ሲያደርጉ ኖረዋል። ከ ዛሬ ሁለት ሺ ዓመታት በፊት በአመራር ላይ ከነበሩ ኦሮሞዎች መሃል እንዲት ሴት እና ወንድ ለመጥቀስ ያህል በመርዌ የነገሠችው የሕንደኬዋ ንግሥት፣ የመደባይዋ ኅሳ ሢያኖን በአፄ ፈንታሌ ጊዜ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራትና የጂማውን ንጉሥ መጋልን እንዘክራለን። ይህም የጂማ ትልቅ ንጉሥ፣ የመደባይን ካህናት ይዞ፣ በአፋር መርከብ ተሳፍሮ ፖርቱጋልን እና ሥፔንን ለ አጭር ጊዜ ከመያዙም በላይ እየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ከአስራ አንድ የኢትዮጵ ዝርያዎች ነገሥታት ወ ጠቢባን ወንድሞቹ ጋር ሆኖ፣ ኢትዮጵያ ግዛት ላይ የታየችውን ኮከብ ተከትሎ ወደ ቤተልሄም ተጒዞ ለዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ ለእየሱስ ክርቶስ ጋዳ እንዳበረከተ ታሪክ ዘግቧል።

ባለፈው 3500 ዓመታት፣ መጀመሪያ በአባታቸው በኢትዮጵ ስርወመንግሥት ስር፣ በኋላም በሰለሞናውያን እና ዛጉዌ ስርወመንግሥት ውስጥ አማራው ያላደረገውን በንጉሥነት፣ በንግሥትነት፣ በንጉሠነገሥትነት እና በንግሥተነገሥታትነት፣ እንዲሁም በባለሙሉሥልጣን እንደራሴነት እና በራስነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን ገዝተዋል። አስተድድረዋል። ለአብነት ያህል፣ ከቅርቦቹ፣ ማለትም ባለፉት 800 ዓመታት ብቻ ዕላይ በተጠቀሱት ማዕረጎች ኢትዮጵያን የመሩ ጥቂት የኦሮሞ ዝርያዎችን እንድጠቅስ ይፍቀዱልኝና የሚከተሉትን ስሞች ላስፍር። --

የሰለሞንን ስርወመንግስት በሸዋ ያስመለሰው የኦሮሞዋ የጊፍቲ መንዲያ ልጅ ንጉሠነገሥት ይኩኖአምላክ፣ እሱም በበኩሉ ኦሮሞዋን ጃን ሞገሳ ዳዲን አግብቶ እሷን የኢትዮጵያ ንግሥተነሥታት አድርጓት፣ የሷ የልጅልጅ አፄ በዕደማርያም ነግሶ የደዋሮውን ኦሮሞ ሙስሊም የገራድ ሞሃመድ በንቲን ልጅ ክርስትና አንስቶ፣ ስሟን "ጃን ክብራ እሌኒ ዳግማዊት" ብሎ ያነገሣት፣ ከዛም በኋላ የሱ እና የሷ ልጅ አፄ ናኦድ አግብቶአት "ናኦደ ሞገሳ እሌኒ ሳልሳዊ" ብሎ ያነገሣት የሃረሩ ሙስሊም ኦሮሞ የቱሉ በዴሳ ልጅ፣ የሱ ልጅ አፄ ልብነድንግል ሕፃን ልጅ ሳለ ደግሞ ኦሮሞዎቹ እናቱ፣ የሴትና የወንድ ኦሮሞ አያቶቹ

እሌኒ ናኦድ ሞገሳ፣ ጃን ክብራ እሌኒ ዳግማዊት እና ቱሉ በዴሳ ሆነው በብስለት፣ በህብረትና በፍቅር መላዋን ኢትይዮጵያን እየመሩ በብቁነት አስተዳድረዋል:: የንግሥት እሌኒ ሞገሳ ወንድም ዶሪ ቱሉ በዴሳ ዘውድ ደፍቶ፣ ባህር-ነጋሽ ተብሎ በቀይ ባህር፣ በትግራይና በአርትራ ነግሦ ነበር:: እሱ ከሞተ በኋላ ደግሞ የእሱ ልጅ ባህር-ነጋሽ ይስሃቅ ዶሪ በሱ ቦታ ነግሦ የእሱን ግዛቶች በሚገባ አስተዳድሯል:: በዚህ አይነት አያሌ ኦሮሞዎች እስከ ፍጻሜ መንግሥት፣ ማለትም የሰለሞን ሥርወመንግሥት ተዳክሞ በዘመነ-መሳፍንት እስከሚተካ ድረስ ኦሮሞዎች ኢትይጵያን ቀጥ አድርገው ገዝተዋል:: ዘመነ-መሳፍንት የተጀመረውም የሊበን ጎሳ በሆነችው በወሎዋ ኦሮሞ ንግሥት ዋቢ ልጅ በ አፄ ኢዮአስ አገዛዝ ጊዜ ነበር:: የሱ እንደራሴ የትግሬው ሥሁል ሚካኤል ተጣሉትና በሻሽ አንቀው ገደሉት:: ከዛ ራሳቸው መንገሥ ስለፈሩ፣ የነገሥታት ልጆች እስኪነግሱ ድረስ ከሚታሰሩበት ከወህኒ-አምባ ዮሃንስ የተባሉ፣ የ 71 ዓመት ድኩም (እጀ-ቆራጣ) ለይስሙላ "በሰለሞን" ዙፋን ላይ አስቀምጠው (አጋድመው ማለት ይሻላል) እሳቸው ንጉስ ሺሚ-ሻሪ ሆነው፣ ከእኘህም ተጣልተው፣ እኚህንም ገለው፣ ሕጻን ልጅ ሾመው እሳቸው በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን አንቀጥቅጠው ገዟት:: ከሳቸው በኋላ ደግሞ የወሎ ኦሮሞዎች ከትልቁ እስከ ትንሹ ራስ አሊ ድረስ እንዲሁ የይስሙላ ንጉሥ አልጋው ላይ እያስተኙ፣ እስከ አፄ ቴዎድሮስ መነሳት ድረስ ገዙ:: ታዲያ ኦሮሞዎች እንደዚህ አድርገው ኢትዮጵያን ሲገዙ አማራዎች ፊንጠር ብለው ቆመው የነሱን መንግሥትና የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በጀግንነት ይጠብቁ ነበር እንጂ ወደዙፋኑ አካባቢ ዝርም አላሉ:: በዚህ አይነት፣ አፄ ቴዎድሮስ አማራ ከተባሉ፣ ካፄ ቴዎድሮስ በቀር አንድም አማራ አልነገሠም ማለት ነው:: አፄ ቴዎድሮስም ቢሆኑ (እዚህ ላይ፣ እሳቸው አማራ ናቸው ብለው የሚኮሩትን ጎንደሬዎች ይቅርታ እየጠየቅሁ) ትልቁ ባለታሪክ አለቃ አጽመጊዮርጊስ <u>የጋላ ታሪክ</u> በሚለው መጽሃፋቸው እንደሚተርኩልን አፄ ቴዎድሮስ አማራ አልነበሩም:: ቋሬ (የቋራ ሰው) ነበሩ እንጂ:: እንደ እሳቸው አባባል፣ ቋሬዎች የራሳቸው ቋንቋ የነበራቸው አማራ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው:: አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውም ቢሁኑ በየማህተማቸው ላይ ፣ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፣ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ) ብለው የአጋዚና የይሁዳ ዘር መሆናቸውን ነበር እያረጋገጡ የሚያውጁት:: በአባታቸው በልጅ ኃይሉ በኩል ቋሬ ቢሆኑም በእርግጥም በእናታቸው በኩል ሰለሞናዊ የነገሥታት ዝርያ ነበሩና:: እሳቸው የጠሩ አማራ ነበሩ ከተባለም እንኳዋን፣ "ንጉሠነግሥት ቴዎድሮስ ዘእምነገደ አምሃራ" ብለው ያላወጁት ከፖለቲካው በተጨማሪ የ አማራ ሥርወመንግሥት ስለአልነበረ ነው:: ይህም የሚጠቁመው አማራ የራሱ ሥርወመንግሥት ኖሮት ኢትይጵያን ገዝቶ እንደማያውቅ ነው:: እስከነአካቴው እሳቸው ይሉት የነበረው "በጋሎች ተይዞ የነበረውን የአባቶቼን የእስራኤላውያንን መንግሥት እግዚአብሄር መለሰልኝ፣" ነበር:: እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት እሳቸው "ጋሎች" ሲሉ መሳደባቸው ሳይሆን በዛን ጊዜ አነጋገር "ኦሮሞ" ለማለት ፈልገው ነው:: እጅግ የሚያፈቅሯት ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች "ጋላ" ነበሩና የሚስታቸውን ወላጆች አይሰድቡም:: ከአፋቸው የፈለቀው ሃቅ ግን ከሳቸው በፊት ኦሮሞዎች ኢትዮጵያን መግዛታቸው ነው:: ታዲያ በኛ ዘመን፣ ኢትዮጵያን በስርወመንግሥት የገዛው አማራ ነው የሚለው ነጭ ውሸት ከየት መጣ? መልሱ ግልጥና ሁለት ነው::-- አንድኛው አማራውን መስፈራርቾ (ፈረንጆቹ እንደሚሉት "ቡጊማን") አድርገው ሥልጣን ለመያዝ ከሚፈልጉ ፖለቲከኞች ብብትና አፍ ይህ ቅጥፈት የወጣ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ የሃገራቸውን ታሪክ ጠንቅቀው ከማያውቁ ጥራዝነጠቅ ግለሰቦች አንደበት የፈለቀ ነው:: ምስኪን አማሮች! ቋንቋቸው ተወዶ የመንግሥት ቋንቋ በመሆኑ እነሱ ገዥዎች መስለው ታዩ:: እነሱ በርግጥ ኢትዮጵያን ገዝተው ቢሆንማ ኖሮ የአማራው ህዝብ ኑሮ ከሌሎቹ እትዮጵያውያን እጅግ የተለየና የተሻለ በሆነ ነበር:: የሚያሳዝነው ነገር፣ ባልዋሉበት ዋሉ፣ ተብለው ተሰቃዩ:: የሆነ ሆኖ፣ በቅርቡና በእኛ ዘመን የነበሩትና የአሉት ኢትዮጵያን የመሩት የኦሮሞ ዝርያዎች ቁጥር እንኳ በዚህ ፅሁፍ ተዘርዝሮ ስለማያልቅ አልፈዋለሁ:: የነሱን ዝርዝር ማየት ከሹ የዛሬ 17 ዓመት አካባቢ <u>ኢትዮጵያን ሪቪው</u> መፅሔት ላይ ያወጣሁትን "ኖብልስ አፍ ኦሮሞ ዲሰንት ሁ ሩልድ ኢትዮጵያ" የተሰኘውን የምርምር ሥራዬን ያጢኑት::

ክቡር ዶ/ር በያና ሱባ፣ ወደ ዐቢዩ ጉዳይ ልመለስና፣ አሁን የወሰናችሁት ውሳኔ መልካም ሲሆን፣ አንድ የማይቀር ዋና ነገር አለ። እሱውም መፃፊያ ፊደላትን የሚመለከት ነው። አሁን ኦሮሞዎች የሚገለገለጉሉበትን የላቲን ፊደላት በሃገር-በቀል ፊደላት ለመተካት ተነጋግራችሁበት ይሆን? መልስዎ አሉታዊ ከሆነ፣ ብትነጋገሩበት ሸጋ ነው። ራሳቸው አውሮፓውያን ካልሆኑ በቀር በላቲን የሚጽፉት የራሳቸው ፊደል የሌላቸው በነጭ ቅኝ ግዛትወይም በባርነት የተገዙ ምስኪን ሰዎች ብቻ ናቸው። እኛ እኮ የራሳችን ፊደል የአለን የተከበርን እና የረቀቅን ሰዎች ነን። የግዕዝ የሚባሉት ሆሄያት የኛ አይደሉም እንደማይሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ከአሉኝም ተሳስተዋል፤ እልዎታለሁ። የግዕዝ ፊደላት የአማራው ወይም የትግሬው ብቻ ከመሰልዎትም አሁንም ተሳስተዋል፤ እልዎታለሁ። ዳሩ የነሱም ብቻ እንኳን ቢሆኑ ከባዕዳኑ የላቲን ፊደላት ይልቅ የሃገራችን ሰዎቹ ሳይቀርበን ይቀራል ይላሉ?

የግዕዝ ፊደላት፣ የዛሬ 3000 ዓመታት የግዕዝ ቋንቋ የበላይነት ከመታወጁ በፊት የነበሩ፣ አማራና ትግሬ ከመፈጠራቸው አስቀድሞ የኖሩ ጥንታዊ ናቸው። ሃቁን ለመናገር፣ ለመፃፊያ እንዲመቹ አድርጎ እንደገና ያነጻቸው፣ የኦሮሞ፣ የአማራና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት የነበረው ታላቁ ንጉስ፣ ሊቀካህናቱና ፈላስፋው ኢትዮጵ ቀዳማዊ ነው። ቀዳማዊ ኢትዮጵ የኖረው የዛሬ 4000 ዓመታት ሲሆን ፊደሎቹ ከዛ ጊዜ በፊት ነበሩ ማለት ነው። ይህም የሚመሰክረው ፊደሎቹ የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ነው። አጋዝያን ከጋዛና ከእስራኤል ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ በፈለሱበት ወቅት ቋንቋቸውን እንጂ ፊደሎቹንም ይዘው ለመምጣታቸው ማስረጃ የለም። ኢትዮጵ የኖረው ከነሱ መፈለስ 1000 ዓመታት አስቀድሞ ነበርና። የግዕዝ ፊደላትን ያመጡት አጋዝያን ናቸው ከተባለም አሁን የሁላችንም ሆነዋል።

ከነዚሁ ከግዕዝ ፊደላት ጎን ለጎን የኦሮሞ ካህናትና ሊቃውንት የተገለገሉባቸው ሌላ እጅግ ጥንታዊ ፊደላትም ነበሩ።-- "የሱባ ፊደላት" የተሰኙ። የመጀመሪያ የሰው (የሰብዕ) ልጆች ቋንቋ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ "ልሳነሰብዕ" ተብሎም ይጠራል። አሁን ያሉትን የግዕዝ ፊደላት ኢትዮጵ ያሻሻላቸው ከሱባ ፊደላት አውጣጥቶ እንደሆነ ይወሳል። የግዕዝ ሆሄያት ከግራ ወደ ቀኝ ሲነበቡ እንደሚታወቀው ሰባት ድምጾች ይሰጣሉ። የሱባ የፊደል ድምጾች ግን እስከ ዐስር ድምጾች ያሰማሉ። ይህን በማድረጋቸውም የሰውን ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮን እና የእንስሳትን ደምጾች ስለሚጋሩ የሱባ ቋንቋ እጅግ የበለጸገ ነበር። የምስራች! ጠፍተው የነበሩት የሱባ ፊደላት ተገኝተዋል። ለአብነት የሚሆኑ ቅጂዎች በኔ በራሴ እጅ ይገኛሉ። እንዲሁም ከስደት ያመለጠ የሱባ እና የ ግዕዝ መዝገበ ቃላት ግልባጭም በእኔ ዘንድ አለ። እነዚህ ሁሉ የጥንት ሊቃውንት አባቶችችን እና አናቶቻችን የተጠቀሙባቸው ናቸው። በ ሱባ ቋንቋ የተከተቡ እሸንክታብ (የ ሚገርመው "ልሳነሰብ" ም ይባላሉ፤) ሞልተዋል። ክታቦቹ ውስጥ ያሉት የማናውቃቸው፣ የድግምት ጽሁፎች የሱባ ቋንቋ ናቸው! በዚሁ በሱባ አሸንክታብ ላይ የተመዘገቡ ጽሁፎችም በሳጥኔ ስውጥ ይገኛሉ። ስለ ግዕዝም እንኳን እንነጋግር ካልን፣ የሚገርምዎት ነገር፣ እኔና እርስዎ አይነቱዎቹ የዛሬ ዘመን ተረናል የምንል ሰዎች "የግዕዝ ፊደላት የኦሮሞኛ ቋንቋን ሊያስተናግዱ ይችላሉ፣ አይችሉም" እያልን ስንከራከር፣ ጥንታዊ አባቶቻችን በግዕዝ ፊደላት የረቀቁ እና የመጠቁ ሃሳቦችን ገልጸውባቸዋል። እኔ እጅ ውስጥ እንኳን ቢያንስ አንድ ሺ ዓመት ሊሆን የሚችል በግዕዝ ፊደላት የተከተበ ብራና ግልባጭ አለ። ይህን ሁሉ መረጃዬን በቅርቡ በማሳትመው የኦሮሞን እና የ አማራን ታሪ ክ በሚያወጋው የእንግሊዝኛ መጽሃፌ ላይ አስመሰክረዋለሁ።

"ሱባ"ን በሚጠቅስ ግን፣ "ለመሆኑ ሱባ የሚባል ነገር አለን? ወይስ ነበረን?" ብሎ የሱባን መኖር ለሚጠራጠር ኦሮሞ ግን፣ ለሱባ መኖር እሩቅ ሳንሄድ ዋናው ምስክር እርስዎ ራስዎ ነዎት። ምክንያቱም፣ ውድ ዶክተር በያና ሱባ ሆይ! ይህን ቃል ርስዎ ራስዎ ተሸክመውት አሉና! ወይም ይህ ቃል ርስዎን ተሸክሞ ይዞራልና! ኦሮሞው አያቶ ለአባቶ ይህን ስም ሲያወጡላቸው የቃሉን ትርገም እና ታሪክ ጠንቅቀው ሳያውቁ እንዳልቀሩ አያጠራጥርም። "ሱባ" ተብለው በዚሁ ስም የተጠሩት አባቶም የስማቸውን ትርጉም አጥርተው እንደሚያውቁ አያጠያይቅም። የ "ሱባን" ትርጉም እና ታሪኩን የማናውቀው እኛ ጥራዝ-

ነጠቆቹ የተማርን ተብዬዎቹ እንጂ እያት ቅድመአያቶቻችን አይደሉም:: የፈረንጅ ዲግሪ አይኑራቸው እንጂ እነሱ በሃገራቸው እውቀት የረቀቁ ናቸው:: ለማንኛውም የ "ሱባ"ን ታሪክ እና ትርጉም እኔና ርስዎ አወቅነውም እላወቅነው፣ አባቶቻችን እንደዘገቡልን፣ የዛሬ 4000 ዓመት ይህን ቃል ለስም መጥሪያ አድርጎ የተጠቀመው አባታችን ኢትዮጵ ነው:: ይህም ኢትዮጵ የኦሮሞዎችም አባት ለመሆኑ አንድ ማስረጃ ነው:: ኢትዮጵ ሶስት ሴቶች ልጆች ወልዶ ነበር:: የአንደኛዋን ስም "ሱባ" ሲል ሰየመው:: የሱ የልጅ ልጅ የሆነው ኢትዮጵ ሁለተኛው ደግሞ እጡብ ድንቅ ከተማ ቆርቁሮ ስሚን "ሱባ" አለው:: በ ኬንያና በ ታንዛኒያ ደግሞ "አባሱባ" የተባሉ፣ ከኢትዮጵያ ሸሽተው የሄዱ ጎሳዎች አሉ:: ኢትዮጵ አስር ወንዶች ልጆች ወልዶ ነበር:: እነዚህ አስሩ ዛሬ ኢትዮጵያውያን ተብለው የሚጠሩት ሁሉ ሕዝቦች አባቶች ናቸው:: ከውንዶች ልጆቹ አንዱን ኢትዮጵ "ቶላ" ብሎ ጠራው:: የኔ የኦሮሞው እጎቴ (የአባቴ ወንድም) ስሙ "ቶላ" ነበር:: ኢትዮጵ የኦሮሞዎችም አባት ለመሆኑ ይህም ሌላ ማስረጃ ነው:: ክቡር ዶክተር በያና ሱባ ሆይ፣ ይህ የኩራትና የክብር ጉዳይ ስለሆነ የላቲኑን ፊደሎች ቋንቋ ለሌላቸው ድሆችና በቅኝ ለተገዙ አሳዝኞች ትተን ጠቢባኑ አባቶቻችን በፈለሰፉት በራሳችን በሱባ ወይም በግዕዝ ፊደላት እንጽፍ ዘንድ የተገባ ነው:: ስለዚህ ርስዎና የአዲሱ ድርጅታችሁ የኦሮሞ ባልደረባዎችዎ ይህን ጉዳይ አበክራችሁ አስቡበት:: የእናንተ መልካም ፍቃድ ከሆነ፣ በዚህ በኩል እኔም ልተባበራችሁ ዝግጁ ነኝ:: በጄ ውስጥ የአሉትንም ስነዶች ለማሳየት ወደ ኋላ አልልም:: ከኢትዮጵ ጀምሮ የነበሩት አባቶቻችን የእኛን በላቲን መጻፍ ቢያዩ ኖሮ አፍረውና አዝነው "እዬዬ!" ብለው ማልቀሳቸው አያነጋግርም::

የዳር ድንበሩና የባንዲራውም ነገር እንደ እዛው ነው:: የኦሮሞዎች፣ የአማራና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት ኢትዮጵ እና ልጆቹ ያቀኑትና ያስፋፉት ምድር በመላው አፍሪካ ብቻ የነበረ ሳይሆን ወደ አረብያ፤ መካከለኛው ምሥራቅና እሥያም የዘለቀና የዘለለ ነበር:: እንዳውም መላው አፍሪካ "ኢትጵያ" ተብሎ ይጠራ ነበር:: ሚል፣ ሚል እየተሸራረፈ ሄዶ አሁን ያለው ኩርማን መሬት ብቻ ተርፏል:: እሱውም ቢሆን አሁንም በየአቅጣጫው እይተሸረሸረ ነው:: የሆነ ሆኖ ሁላችንም የኢትዮጵ ልጅ እንደመሆናችን መጠን አገራችን መላዋ ኢትዮጵያ እንጂ ኦሮምያ ተብላ በቀደም እለት የተጠራች ጭራ-ቀንዲ የት ጋ እንዳለ ያልተረጋገጠና የተወሳሰበ ኩርማን መሬት አይደለችም:: ስለዚህ "ኦሮምያ" በተባለችው ጠባብ ስፍራ ከመኮራመት ይልቅ በሁዳድዋ ኢትዮጵያ ወርድና ስፋት ላይ መቦረቅ ይገባናል:: ክብርነትዎ በዚህ የብልህነት እሳቤ እንደሚስማሙ አልጠራጠርም::

የሃገራችንን ባንዲራ "ሠንደቅአልማ" ሲል ሰይሞ የዛሬ 3400 ዓመታት የፈጠራት ስመ-መንግሥቱ ሠንደቅአልማ ተብሎ ይጠራ የነበረው ግንደዘራችን የኢትዮጵ ሽንት አጼ እስያኤል ነው:: የነጻነት አርማና የኢትዮጵያዊነት ክብር ተብላ በንጎሦች ሰረገላዎችና ቤተመንግሥቶች፣ እንዲሁም በጦር ሜዳዎች ትውለብለብ ብሎ አዘዘ:: እሱ የመረጣቸው ቀለማት አረንጓዴ፣ ቢጫና ሰማያዊ ነበሩ:: በሰማያዊው ፈንታ አሁን ቀይ ተተክቷል:: ስለዚህ የኦሮሞ ዝርያ የሆንን ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ የኛም መሆንዋን አውቀን በኩራት ልናውለበልባት ይገባል:: አደራዎን-- ርስዎ እና ተባባሪዎችዎ ሆናችሁ የባንዲራዋን ነገር አስቡበት:: ይህች የነፃነት ሰንደቅአላማ አየር ላይ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ አያሌ የኦሮሞ ጀግኖች ባለፉት 3400 ዓመታት በደማቸው መሥዋዕትነት ከፍለውላታል:: እኛ የአሁኖቹ ትውልድ ይችን ሠንደቅአላማ አክብረን መውደድና እሷ በነፃነት ዐየር ላይ ትውለበለብ ዘንድ በተራችን ራሳችንን መሰዋት ግዴታችን ነው::

እላይ ከተጠቀሱት ጉዳይዎች የማያንሰው ወይም የሚልቀው የኦሮሞውችና የአማራዎች ግንኙነት ነው:: ኦሮሞዎችና አማሮች የመነጩት የዛሬ 3600 ዓመት አካባቢ ደሸት ከተባለ ነቢይና ፈላስፋ አብራክ ነው:: ቦታውም ጎጃም ነበር:: ደሸት ጂማን፣ ማጂን፣ መደባይን እና መንዲን ወለደ:: ጂማ ማራን (አማራን) እና ጃማን (ጃማካንስ ወይም ጃሜካንስ የጃማ ልጆች ናቸው፣) ወለደ:: መደባይ፣ ጂማና መንዲ የኦሮሞዎችና የሌሎቹ ኢትዮጵያውያን አባቶች ሆኑ:: ኦሮሞ "ኦሮሞ" መባል የጀመረው የዛሬ 3000 ዓመት፣ በቀዳማዊ ምኒልክ

ዘመንመንግሥት ነበር:: ከዛ በፊት ግን ዋናዎቹ ኦሮሞዎች መደባይ ተብለው ይጠሩ ነበር:: አሁንም ድረስ በዚህ ታላቅ ስም የሚጠሩ ኢትዮጵያውያን በጎጃም፣ በጎንደር በትግራይና በሌሎችም ቀዬዎች ይገኛሉ:: የዚህን ዝርዝር ወደፊት አቀርበዋለሁ:: ኦሮሞዎችና አማሮች ከውጭ ሃገር አልፈለሱም:: ጎጃም-ፈለቅ፣ ኢትዮጵያ-በቀል ናቸው:: ኦሮሞዎች የኢትዮጵያን ዳርድንበር ዘለው የመጡ ፈላስያን ወይም ወራሪዎች ናቸው፣ የሚባለው ነጭ ውሸት ነው:: ርግጥ ኦሮሞዎች ሃገርና ጀብድ ፍለጋ ከኢትዮጵያ እየተነሱ መላዋን አፍሪካ እያሰሱ የተወሰኑት ወደ ኢትዮጵያ እንደ ገና ይመለሱ ነበር:: አንዳንዶቹ ደግሞ እዛው እሄዱበት ስፍራ ተመቻችተው ይቀሩ ነበር:: ከሃገር ወጥተው ከቀሩት ከእነዚህ የኦሮሞ ዝርያዎች መካከል በኬንያ የሚኖሩት የኪኩዩና የማሳይ ጎሳዎች እና ርስታቸውን በሩዋንዳ ያደላደሉት ቱትሲዎች ይገኙባቸዋል:: በማዳጋስካርም ቀልጠው የቀሩ ኦሮሞዎች አሉ:: ለመደምደም ያህል፣ ኦሮሞዎችና አማሮች እንደሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ካንድ ደም የተቀዱና ካንድ አጥንት የተቀመሙ ናቸው:: ይህን ሃቅ ግንዛቤ ውስጥ በመክተት ያለፈውን አለመግባባትና ግጭት ወደ ጎን ትቶ የወደፊቱ ህብረት፣ ፍቅርና ሰላም ላይ ማተኮር ይገባል::

በመጨረሻም፣ ርስዎን እና ድርጅትዎን የምመክራችሁ፣ እውነተኛው የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ፣ የዘር ሃረግና ባህል እንደገና ተጤኖ ይታወቅ ዘንድ አንድ የጥናትና የምርምር ማዕከል ወይም ተቋም እንድታቋቁሙ ነው:: ይህም ማለት፣ የፖለቲካው ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው:: ይህ ተቋም፣ እውነቱን ከውሸቱ፣ ሃቁን ከተረቱ፣ ፈንጠዝያውን ከገሃዱ እውነታ ለይቶ የአእምሮ ውዥንብርን ያበናል፣ ያተናልና:: ከዚህ ተቋም ተግባር አንዱ ማንነታቸውን የተወናበዱትን ኦሮሞዎች እውነተኛ ማንነት፣ ማለትም ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው:: በሚኖሰታ፣ በሌሎቹ ዩናይትድ ስቴቶች፣ በካናዳ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአፍሪካ እና በኢትዮጵያም ጭምር የሚኖሩ በርካታ ኦሮሞዎች ከዚህ ቀደም "ኢትዮጵያውያን አይደላችሁም፣" ተብለው፣ ሃሰት ተነግረው፣ የማንነት ቀውስ (አይዴንቲቲ ክራይዚስ) እንደደረሰባቸው እሙን ነው:: ይህን የማንነት ቀውስ ማስተካከል እንዳውም የድርጅታችሁ ቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት:: ይህ የማንነት ቀውስ ባሰቸኳይ መፍትሄ እስካላገኘ ድረስ ለሥራችሁ እንቅፋት ይሆንባችኋልና:: ከዚህ በተረፈ፣ አዲሱ አቋማችሁና ግንባራችሁ ለኦሮሞ ሕዝብ፣ ብሎም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሰላምና እድገት እጅግ ጠቃሚ ናቸውና በርቱባቸው:: በዚህ በተቀደሰ አላማችሁ ውስጥ እግዚአብሄር ገብቶበት ይርዳችሁ:: ያለ እግዚአብሐር እርዳታ የሰው ድካም ሁሉ ከንቱ ነውና::

ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ፣
ዘብሄረ ኢትዮጵያ፣
ኢልማ ኢትዮጵ ንጉሠነገሥት ዘ ኢትዮጵያ፣
ኢልማ ደሸት፣ ነቢይ፣ ፈላስፋ፣ ሊቀካህን፣ ወ ንጉሠ ጎጃም::

እኤአ ግንቦት 24 ቀን 2013፣
ካሊፎርንያ

ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ፣ ጂግሳ፣ በ lulu.com or Amazon.com የሚገኘው የ **The Hidden and Untold History of the Jewish People and Ethiopians** ደራሲ ነው::
ለደራሲው አስተያይት መለገስ ካማረዎ በ **ftolossa@aol.com** ኢሜል ያድርጉለት:: ጊዜ ካለው ይመልስልዎታል:: ዌብ ሳይቱን ለመጎብኘትና አንዳንድ ጽሁፎቹን ለማንበብ ካማረዎ ወደዚህ ይሂዱ.. **Fikretolossa.com**